# የልማት እቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ደጋፊ የስራ ሂደት

<u>የስራ ሂደቱ መጠሪያ፡-</u> የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ደጋፊ የሥራ ሂደት

## የስራ ሂደቱ ትርጓሜ

የልማት እቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ የሥራ ሂደት ማለት በመንግስት፣ በዕርዳታና ብድር በጀት፣ በህብረተሰቡ የሚከናወኑ የፐብሊክ ሴክተር አቅም ግንባታ ስራዎች የክልሉን የልማት ፖሊሲን መነሻ ባደረገው እቅድ እንዲመሩና ክትትልና ግምገማ ተደርጎባቸው በአግባቡ ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚሰጡ አገልግሎቶችና ተግባራትን የመፈፀም ሀላፊነት የተሰጠው የመንግስት አስፈፃሚ አካል ማለት ነው፡፡

## የስራ ሂደቱ ዓላማ

የቲሙ ዓላማ ከጊዜ፣ ከወጪና ከጥራት አንፃር የደንበኞችን/የተገለልጋዮችን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስችሉ የልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥራዎችን በማከናወን የሚጠበቁ ዉጤቶችንና የግብ ስኬት ማምጣት ነው፡፡

<u>ዓላማ፡-</u> በዞኑ ዉስጥ የሚከናወኑ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች በመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ ተመስርተው፣ በተቀናጀና ሁሉ አቀፍ በሆነ እቅድ የሚመሩበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡

## የስራ ሂደቱ ባህሎች(Norms)፣ ዕሴቶችና (Values) ዕምነቶች(Beliefs)

- ተገልጋይ ተኮር የመስጠት ልምድ፣
- በመራሄ ሙያ የመስራትና ችግሮች የመፍታት ዝንባሌ
- በቲም ስሜት አብሮ የመስራት ባህል፣
- ለተገልጋይ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ልምድ፣
- ዉጤት ለማምጣት የመጣር ዝንባሌ፣
- ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን የመቀበል ዝግጁነት፣
- ተነሳሽነትና በራስ መተማመን ባህል፣
- አዳዲስ ዕዉቀቶችን የመሻት፣ የመማርና የመለወጥ ባህል፣

## የስራ ሂደቱ ከሌሎች መ/ቤቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ግንኙነት

| ግንኙነት የሚደረግባቸው መ/ቤቶችና ባለድርሻ አካላት | የግንኙነቱ ምክንያት | የግንኙነቱ መንገድ |
|---|---|---|
| በዞኑ በተለያዩ አስተዳደር እርከኖች ካሉ አቅም ግንባታ ፕሮግራሞችና ፈፃሚ መ/ቤቶችና አስቀጣይ ተቋማት | ▪ የእቅድ ዝግጅት፣የክትትልና ግምገማ ስራዎችን በጋራ በማከናወን<br>▪ መረጃዎች በወቅቱ በመለዋወጥ<br>▪ በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ ቴክኒካል ድጋፍ<br>▪ በማስፈፀሚያ ፕሮጀክቶች ዝግጅት ግምገማና በጀት ድጋፍ | ▪ በሪፖርትና ግብረ-፣መልስ<br>▪ በአዉደ ጥናት<br>▪ በመረጃ መረብ<br>▪ በስልጠና መድረኮች |
| በዞኑ በተለያዩ አስተዳደር እርከኖች ያሉ ወረዳ አቅም ግንባታ ሴክተር የሥራ ሂደቶችና መ/ቤቶች | ▪ በ5 ዓመት እና በአመታዊ እቅድ ዝግጅት፣ በፕሮጀክት ብቃት ግምገማ፣ የፕሮጀክቶችን የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ስራ በጋራ ተሳትፎ በመስራት<br>▪ ለፕሮጀክት አፈፃፀም ተፈላጊ አገልግሎት በመስጠት<br>▪ በመረጃ ልዉዉጥ<br>▪ በማስፈፀሚያ ፕሮጀክቶች ዝግጅት ግምገማና በጀት ድጋፍ | ▪ በቢሮ በአካል በመገናኘት<br>▪ በጋራ ስብሰባዎችና በአዉደ ጥናቶች<br>▪ በዓመታዊ የጋራ ፎረም<br>▪ በመረጃ መረብና ሌሎች መገናኛ ቴክኖሎጂዎች |
| ከዞኑ ም/ቤት | ▪ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሪፖርቶችን በማጠቃለልና ለዉሳኔ አመቺ በሆነ መልኩ በማቅረብ<br>▪ እቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም አስፈላጊ መረጃዎችን መለዋወጥ | ▪ በጋራ ስብሰባዎች<br>▪ በወቅታዊ ሪፖርቶችና የጋራ ዉይይት መድረኮች |
| ከአበዳሪና ረጂ ድርጅቶች፣ ከክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ፣ ከሌሎችም የሚመለከታቸው ተቋማትና ባለድርሻ አካላት | ▪ ተፈላጊ መረጃዎችን በመለዋወጥ<br>▪ በባለሙያ አቅም ግንባታ<br>▪ በብድርና እርዳታ ለሚከናወኑ የመንግስት ፕሮግራሞች ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ<br>▪ በማስፈፀሚያ በጀት ድጎማ | ▪ በጋራ ስብሰባዎች<br>▪ በደብዳቤ ልዉዉጥ<br>▪ በመደበኛ የፕሮግራም አፈፃፀም ሪፖርቶች<br>▪ በመረጃ መረብ |

## በስራ ሂደቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችና ተግባራት

- የረጅምና የመካከለኛ ዘመን የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች የፊሲካል እቅዶችና በጀት ማዘጋጀትና መከለስ፤
- የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችንና የሴክተሩን አመታዊ እቅድ፣የድርጊት መርሃ ግብር፣በጀት፣የአፈጻጸምና የተሳትፎ ስምምነት እና የግዥ እቅድ ዝግጅት ማስተባበር፣መጠናከርና ማጸደቅ አፈጻጸማቸውን መከታተል፤
- የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ፕሮጀክቶችን መገምገም፣ በመስክ ክትትል ማድረግ፣የቴክኒክ ድጋፍ መስጠትና ማጸደቅ፤
- ለአቅም ግንባታ ለሚቀርብ ጥናት ሰነድ/አዉደ ጥናት ጥያቄ ላይ መሳተፍ፣ በተዘጋጀው መመሪያና ማኑዋል ላይ ስልጠና መዉሰድ፣
- የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን እቅድ አፈጻጸም መከታተል፣ድጋፍ መስጠት፣መገምገምና ሪፖርትና ግብረመልስ ማዘጋጀት፤
- የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን የእርዳታና ብድር በጀት ማቀድ፣ ፕሮፖዛል መስራት፣ ማስተባበርና መከታተል፤
- በግማሽ ዘመን የአፈጻጸም ግምገማ ውጤት መሰረት የቀጣዩን ግማሽ አመት የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች እቅድ እንደ አስፈላጊነቱ ክለሳ በማድረግ የተከለሰ የልማት እቅድ ያዘጋጃል፤